# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## የስብከት ዘመን ሦስተኛ ሰንበት

ከታህሣሥ ፯ ቀን ጀምሮ እስከ ታህሣሥ ፳፯ ቀን ያለው ዘመን ዘመነ ስብከት ይባላል። ምክንያቱም ነቢያት የጌታን በሥጋ መምጣት አምልው አስፍተው በትንቢት በትምህርት በማስተማር መስበካቸውን ቤተ ክርስቲያን እያሰበች ሰውን ለማዳን ወደ ምድር የመጣውን አምላክ የምትሰብክበት ወቅት በመሆኑ ነው።

### የዕለቱ ምስባክ

ኖላዊሆሙ ለእስራኤል አጽምዕ
ዘይርዕዮሙ ከመ አባግዐ ዮሴፍ
ዘይነብር ዲበኪሩቤል አስተርአየ

የእስራኤል ጠባቂ ሆይ አድምጥ
ዮሴፍን እንደመንጋ የምታሰማራ
በኪሩቤል ላይ የተቀመጠው (የምትቀመጠው) ተገለጠ
(ተገለጥ) መዝ ፸፱፡፩

ምስጢር (ትርጉም)፥ የእስራኤል ዘነፍስ (ምእመናን) ጠባቂ ስማ፤ የዮሴፍ በጎች ይጠበቁ (ዮሴፍ ይጠብቅ) እንደ ነበር ክርስቲያኖችን የምትጠብቅ ስማ፤ በአብ ቀኝ በኪሩቤል ላይ የሚኖር እውነተኛ የበጎች እረኛ እኔ ነኝ ሲል (ስትል) በሥጋ ተገለጠ (ተገለጥ) ማለት ነው።

ወንጌል፥ ዮሐ ፲፡፩-፳፪
ቅዳሴ፥ የጌታችን (ነአኵተከ)

የዘመነ ስብከት ሦስተኛ ሰንበት ኖላዊ ይባላል። ኖላዊ ማለት እረኛ ማለት ሲሆን ነቢያት እውነተኛ እረኛ ሆኖ የእግዚአብሔር ልጅ ይገለጣል ብለው መተንበያቸውን እና ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ እረኛ መሆኑን [ቤተ ክርስቲያናችን] እያሰበች የምትዘምር የምትቀድስ የምታመሰግንበት ዕለት ነው።

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ዕብ ፲፫፡፲፯ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ጴጥ ፪፡፳፩ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፲፩፡፳፪ እስከ ፍጻሜ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

### የዕለቱ ትምህርት

#### ኢየሱስ ክርስቶስ እረኛችን ነው።

«መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለበጎቹ ያኖራል። እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኩላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል። ሞያተኝ ስለሆነ ለበጎቹም ስለማይገደው ሞያተኛው ይሸሻል። መልካም እረኛ እኔ ነኝ፥ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ» (ዮሐ ፲፩-፲፭) እንዳለ ጌታችን። እረኛ ለቤተ ክርስቲያን እርሱ ነው። እንደ ቅጥረኛ እረኛ በጎችን በማሰማራት ፈንታ ወደ እረፍት መስክ (መዝ ፳፪፡፩-፪) እራሱን ያላሰማራ፤ በአደራና በጠባቂነት የተሰጧቸውን በጎች እያረዱ እየበሉ አውሬ በላቸው እንደሚሉ ቅጥረኞች ያይደለ፤ እረኞች በጎች እስከሚበርዳቸው ድረስ ያለ አግባብ ጠጉራቸውን እንደሚሸልቱ ቅጥረኛ ያልሆነ፤ ታማሚ በጎችን እንዳላከሙ፣ ደካማዎችን እንዳላዳኑ፣ ሰባራዎችን እንዳልጠገኑ፣ የጠፉትን በጎች ወደ መንጋው በመመለስ ፈንታ ወሬያቸውን በመሰለቅ በወንበራቸው ተቀምጠው እንዳልሰበሰቡ እረኞች ያይደለ የጠፉትን የሚሰበስብ እረኛ ነው።
የሰቡትና የወፈሩት አንዳንድ በጎች ምስኪኖችን እና የከሱትን በጎች እየገፉ ከበረት ሲያስወጡአቸው በቀንዳቸው ሲወጉዋቸው ሲያቆስሏቸው ሲያደሙአቸው የሚጠጡትን ውሃ ሲያደፈርሱባቸው ምግባቸውን ሲረግጡባቸው እያዩ ከመቀመጫቸው ላለመነሳት ዝም ብለው እንደሚያዩ ቅጥረኞች ያይደለ እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

«እግዚአብሔር እረኛዬ ነው የሚያሳጣኝም የለም። በለመለመ መስክ ያሳድረኛል» (መዝ ፳፪፡፩-፪) ተብሎ እንደተጻፈ ወደለመለመ መስክ ወደ ወንጌል ወደ እረፍተ መንግሥተ ሰማያት ይመራልና ኢየሱስ ክርስቶስ እረኛችን ነው። «ይህንም ምሳሌ ነገራቸው እንዲህ ሲል፥ መቶ በግ ያለው ከእነርሱም አንዱ ቢጠፉ ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ የጠፋውን እስኪያገኝ ድረስ ሊፈልገው የማይሄድ ከእናንተ ማን ነው? ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከመዋል፤ ወደ ቤቱም በመጣ ጊዜ ወዳጆቹንና ጎረቤቶቹን ባንድነት ጠርቶ የጠፋውን በጌን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ያላቸዋል። እላችኋለሁ እንዲሁ ንስሐ ከሚያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል። (ሉቃ ፲፭፡፫-፯) ተብሎ እንደተጻፈ ከባዘንበት ምድረ በዳ፤ ከጠፋንበት ውድማ ይፈልገናል፤ ያገኘናል፤ በደረቱም ይታቀፈናል፤ በትከሻውም ይሸከመናል፤ ወደመንጋው ይሰበስበናል፤ ይቀላቅለናል። ቅዱስ ዳዊት በእረኝነቱ ለበጎቹ ሲል እንዴት ከአራዊት ጋር እንደታገለ በጎቹንም በምን ዓይነት መንገድ ከአራዊት መንጋጋ እንዳስጣለ «ዳዊትም ሳኦልን አለው፥ እኔ ባሪያህ የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሳና ድብ ይመጣ ነበር። ከመንጋውም ጠቦት ይወስድ ነበር። በኋላውም እከተለውና እመታው ነበር ከአፉም አስጥለው ነበር። በተነሳብኝም ጊዜ ጉሮሮውን ይዜ እመታውና እገድለው ነበር (፩ኛ ሳሙ ፲፯፡፴፬-፴፭) የተባለውን እንገንዘብ። ዳዊት በጎቹን ታግሎ እንዳዳነ እኛንም እረኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዲያቢሎስ ጉሮሮ ከአንበሳ መንጋጋ አድኖናል፤ ወደፊትም ይጠብቀናል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።